# የሾሉ ዕቃዎችን ማስወገድ

## የሾሉ/ስለታማ ዕቃዎች ምንድን ናቸው?

የሾሉ ዕቃዎች የሚባሉት ጥቅም ላይ የዋሉ ስሪንጆች፣ መርፌዎች፣ ሊነጣጠሉ የሚችሉ የኢንሱሊን ብዕር መርፌዎች እና መርፌ ከመስጠት በኋላ የሚተርፉ ብልቃጦች ናቸው። በቤት ውስጥ መርፌ የሚሰጡ ከሆነ ሹል ዕቃዎችን እንዴት በአስተማማኝና በሕጋዊ መንገድ ማስወገድ እንደሚችሉ ማወቅ አለብዎት።

## ያገለገሉ የሾሉ ዕቃዎቼን እንዴት ማስወገድ እችላለሁ?

በቤት አካባቢ ጥቅም ላይ እንዲውል የተፈቀደ “የሹል ዕቃዎች መያዣ” እንዲጠቀሙ እንመክራለን (ከዚህ በታች ይመልከቱ)። ሹል ዕቃዎች በሽታን የሚያስከትሉ ጀርሞች ሊኖሩት የሚችል ደም ሊይዙ ይችላሉ። በብዙ ካውንቲዎች/ከተሞች ውስጥ በቤት ውስጥ ቆሻሻ መጣያ ውስጥ ሹል ዕቃዎችን መጣል በሕግ የተከለከለ ነው።

ሹል የሆኑ ዕቃዎችን በዘፈቀደ በቆሻሻ መጣያ ውስጥ አይጣሉ ወይም ወደ መጸዳጃ ቤት ውስጥ አይጨምሩ።



**1.** ምን ዓይነት የማስወገጃ መያዣ ተቀባይነት እንዳለው ይወቁ።

በመጀመሪያ ከተማዎን ያረጋግጡ፣ ከዚያም ካውንቲው የሹል ዕቃዎች አወጋገድ ደንቦች እንዳሉት ያረጋግጡ። የተፈቀደለት የሹል ዕቃዎች መያዣ የተሻለ ቢሆንም አንዳንድ ከተሞች እንደ ባዶ ፕላስቲክ የሳሙና ጠርሙሶች ያሉ ጊዜያዊ መያዣዎችን መጠቀም ይፈቅዳሉ።




**2.** ¾ ሙሉ መያዣ ያዘጋጁ እና ይዝጉ። ተቀባይነት ወዳለው የቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ ይውሰዱት (ቀጣዩን ገጽ ይመልከቱ)።

ወይም በከተማዎ ከተፈቀደ የተዘጋጀውን መያዣ በቤት ውስጥ ቆሻሻ መጣያ ውስጥ ይጣሉ።

የሲያትል ከተማ እና የSnohomish ካውንቲ በሙሉ ማንኛውም ዓይነት ሹል እቃ በቆሻሻ መጣያ ውስጥ እንዲጣል አይፈቅዱም።




## የሹል እቃ መያዣዎች ምንድን ናቸው?

የሹል ዕቃ መያዣዎች ብዙውን ጊዜ ቀይ የፕላስቲክ መያዣዎች ሲሆኑ ይዘታቸው አደጋ ሊያስከትል እንደሚችል ለመለየት “sharps/ሹል/” የሚለው ቃል እና የባዮሎጂያዊ አደጋ ምልክት ያለባቸው ናቸው (በቀኝ በኩል ያለውን ፎቶ ይመልከቱ)። በቤት ውስጥ ያገለገሉ ሹል ዕቃዎችን ለመሰብሰብና ለማከማቸት ይህ በጣም አስተማማኝ ዘዴ ነው።



## ቀይ የሹል ዕቃዎች መያዣ ከየት ማግኘት እችላለሁ?

ፋርማሲዎች፦ የልጅዎን መድሃኒቶችና መርፌዎች የሚያገኙበትን ፋርማሲ ያነጋግሩ። ብዙዎቹ ፋርማሲዎች የሹል ዕቃዎች መያዣዎችን ይሸጣሉ ወይም ለደንበኞች ይሰጣሉ። የSeattle Children’s Ocean እና Forest የተመላላሽ ታካሚ ፋርማሲዎች ለመጀመሪያ ጊዜ መርፌዎችን ወይም ሲሪንጆችን ለሚወስዱ ታካሚዎች የሹል ዕቃዎች መያዣዎች አሏቸው።

በይነመረብ፦ **sharpsdisposal.com**ን ይመልከቱ ወይም በአነስተኛ ክፍያ የሹል ዕቃዎች መያዣዎችን እና የማንሳት አገልግሎት የሚሰጡ የመልሶ-መላክ ፕሮግራሞችን በድር ላይ ይፈልጉ።

የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎ፦ የልጅዎን የጤና እንክብካቤ አቅራቢ መያዣውን ከየት እንደሚያገኙ እና ሲሞላ የት እንደሚጥሉ ይጠይቁ።



**ተጨማሪ ለማወቅ**

- Ocean ፋርማሲ 206-987-2138
- የልጅዎን የህክምና አቅራቢ ይጠይቁ
- **seattlechildrens.org**

**ነጻ የአስተርጓሚ አገልግሎቶች**

- በሆስፒታል ውስጥ ከሆነ፣ ነርስዎን ይጠይቁ።
- ከሆስፒታል ውጪ ለሆነ ቦታ፣ ወደ ነጻ የቤተሰብ የትርጉም አገልግሎት ስልክ መስመር በ 1-866-583-1527 ላይ ይደውሉ። ለአስተርጓሚዉ የሚፈልጉትን ስም ወይም የውስጥ መስመር ይንገሩ።

Seattle Children’s®
HOSPITAL • RESEARCH • FOUNDATION

| | |
|---|---|
| **መያዣዬን ለመጣል እንዴት ማዘጋጀት እችላለሁ?** | • በሹል ዕቃ መያዣው ላይ የተሰጡትን መመሪያዎች በሙሉ በመከተል መያዣውን ይዝጉ እና ያሽጉ። ጊዜያዊ መያዣ (ባዶ ፈሳሽ የልብስ ማጠቢያ ሳሙና ኮዳ) የሚጠቀሙ ከሆነ ክዳኑን በፕላስተር በጥብቅ መለጠፍዎን እርግጠኛ ይሁኑ።<br>• ማንኛውም ጊዜያዊ መያዣ ላይ "sharps" ወይም "biohazard" የሚሉትን ቃላት በትልቁ ይጻፉ። |

## በዋሽንግተን ስቴት ውስጥ የሹል ዕቃዎች ማስወገጃ ጣቢያዎች ያሉበት ቦታ

እያንዳንዱ ከተማ/ካውንቲ ሹል ዕቃዎችን ለማስወገድ የተለያዩ አማራጮች አሉት። በከተማዎ ውስጥ ምን ዓይነት አማራጮች እንዳሉ ማወቅ ያስፈልግዎታል። በአሜሪካ ዙሪያ ደህንነቱ የተጠበቀ የመርፌ አወጋገድ ላይ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት **safeneedledisposal.org**ን ይጎብኙ። የእርስዎን የማስወገጃ አማራጮች እና መጣያ ጣቢያዎች ለማግኘት የዚፕ ኮድዎን ያስገቡ።

የሲያትል ከተማ የደረቅ ቆሻሻ መልሶ ጥቅም ላይ ማዋል እና አወጋገድ መረጃ መስመር
206-684-8400

- የሲያትል የሹል እቃዎች መሰብሰብ ፕሮግራም (Seattle Sharps Collection Program) መጣያ ጣቢያዎች
  **seattle.gov/utilities/protecting-our-environment/safe-and-clean-seattle/sharps-collection**
- የሰሜን ሪሳይክል እና ማስወገጃ ጣቢያ (North Recycling and Disposal Station) – 1350 North 34th Street
  (በFremont/Wallingford አካባቢ የሚገኝ)
- ደቡብ ሪሳይክል እና ማስወገጃ ጣቢያ (South Recycling and Disposal Station) – 130 South Kenyon Street

የኪንግ ካውንቲ የህብረተሰብ ጤና **(King County Public Health)**

- የመርፌ ልውውጥ ፕሮግራም (Needle Exchange Program) 206-263-2000
- ሹል ዕቃዎችን ደህንነቱ በተጠበቀ እና ሕጋዊ በሆነ መንገድ ማስወገድ
  **kingcounty.gov/sharps**

**Snohomish** ካውንቲ የደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር የሹል ዕቃዎች አወጋገድ
በካውንቲው የቆሻሻ መሰብሰብ ወይም የማስተላለፊያ ጣቢያዎች በኩል የሚቀርብ ምንም የማስወገጃ አገልግሎት የለም። ወደ **safeneedledisposal.org/states/Washington/** ይሂዱ ለማውረጃ ፋርማሲዎች ዝርዝር ዚፕ ኮድዎን ያስገቡ።

ለሌሎች ካውንቲዎች የሹል ዕቃዎች ማስወገጃ ጣቢያዎች፣ የዋሽንግተን ስቴት የጤና መምሪያ **(Washington State Health Department)** ድረ-ገጽን ይመልከቱ፡
የአካባቢዎን የጤና መምሪያ (የአስተዳደር ወሰን) ለማግኘት በካውንቲዎ ላይ ጠቅ ያድርጉ፡
**doh.wa.gov/AboutUs/PublicHealthSystem/LocalHealthJurisdictions**
እነዚህን ቁልፍ ቃላት ይጠቀሙ፡- sharps disposal፣ needle exchange programs፣ biohazard waste disposal፣ safe needle disposal፣ metro[city].gov፣ recycling and disposal stations።

Seattle Children's መስማት ለተሳናቸዉ፣ መስማት ለሚቸገሩ ወይም ከእንግሊዝኛ የተለየ ቋንቋ ለሚናገሩ ታካሚዎች፣ የቤተሰብ አባላትና የህግ ተወካዮች፣ ነጻ የአስተርጓሚ አገልግሎቶች ይሰጣል። በጥያቄ መሰረት Seattle Children's ይህን መረጃ በአማራጭ ፎርማቶች እንዲገኝ ያደርጋል። ለቤተሰብ ሃብት ማዕከል በ206-987-2201 ላይ ይደዉሉ። ይህ የመረጃ መስጫ ጽሁፍ በSeattle Children's ክሊኒካል ሰራተኞች ተገምግሟል። ነገር ግን፣ የእርስዎ ፍላጎቶች ልዩ ናቸዉ። ወደተግባር ከመግባትዎ ወይም በዚህ መረጃ ላይ ከመደገፍዎ በፊት፣ እባክዎ የእርስዎን የጤና እንክብካቤ ሰጪ ያነጋግሩ።

11/22
PE612AM

© 2024 Seattle Children's, Seattle, Washington. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነዉ።

# Disposal of Sharps

## What are sharps?

Sharps are used syringes, needles, detachable insulin pen needles, and vials left over after giving injections. If you give injections at home, you need to know how to dispose of your sharps safely and legally.

## How do I dispose of my used sharps?

We recommend that you use an approved "sharps container" in the home setting (see below). Sharps can carry blood that may have germs that cause disease. In many counties/cities, it is against the law to throw away sharps in household garbage cans.

**Never throw sharps loosely into the trash or flush them down the toilet.**



**1. Know what disposal container is acceptable.**

Check with your city first, then county to see if it has sharps disposal rules. While an approved sharps container is best, some cities allow the use of makeshift containers like empty plastic detergent bottles.




**2. Prepare and seal ¾ full container. Take it to an approved disposal location (see next page).**

**Or dispose prepared container in the household trash bin if allowed by your city.**

The city of Seattle and all of Snohomish County **do not** allow any kind of sharps disposal in a trash bin.




## What are sharps containers?

Sharps containers are usually red plastic containers labeled with the word "sharps" and a biohazard symbol to identify the contents as a potential danger (see photo on right). This is the safest method for collecting and storing used sharps in the home.



## Where can I get a red sharps container?

**Pharmacies:** Check with the pharmacy where you get your child's medicines and syringes. Many pharmacies sell sharps containers or provide them for customers. Seattle Children's Ocean and Forest Outpatient Pharmacies have sharps containers for patients picking up needles or syringes for the first time.

**Internet:** Check sharpsdisposal.com or search the web for mail-back programs that provide sharps containers and pick-up service for a small fee.

**Your health care provider**: Ask your child's healthcare provider where to get one and where to dispose of a full container.



### To Learn More

- Ocean Pharmacy 206-987-2138
- Ask your child's healthcare provider
- seattlechildrens.org

### Free Interpreter Services

- In the hospital, ask your nurse.
- From outside the hospital, call the toll-free Family Interpreting Line, 1-866-583-1527. Tell the interpreter the name or extension you need.

Seattle Children's®
HOSPITAL • RESEARCH • FOUNDATION

## How do I prepare my container for disposal?

- Follow all directions on the official sharps container to close and seal it. If you are using a makeshift container (empty liquid laundry detergent jug), be sure to tape the lid securely.
- Label any makeshift container with the big words "sharps" or "biohazard."

## Locations for sharps disposal stations in Washington state

Every city/county has different options for sharps disposal. You will need to find out what options are offered in your city. For more information on safe needle disposal around the U.S., visit **safeneedledisposal.org**. Enter your zip code to find your disposal options and drop off sites.

**City of Seattle Solid Waste Recycle and Disposal Information Line**
206-684-8400

- Seattle Sharps Collection Program drop sites
  **seattle.gov/utilities/protecting-our-environment/safe-and-clean-seattle/sharps-collection**
- North Recycling and Disposal Station – 1350 North 34th Street (Located in the Fremont/Wallingford area)
- South Recycling and Disposal Station – 130 South Kenyon Street

**King County Public Health**

- Needle Exchange Program 206-263-2000
- Safe and legal disposal of sharps
  **kingcounty.gov/sharps**

**Snohomish County Solid Waste Management Sharps Disposal**
No disposal service through the county garbage pick-up or transfer stations. Go to **safeneedledisposal.org/states/Washington/** Enter your zip code for a list of drop off pharmacies.

**For other counties' sharps disposal sites, see the Washington State Health Department website:**
Click on your county to find your local health department (jurisdiction):
**doh.wa.gov/AboutUs/PublicHealthSystem/LocalHealthJurisdictions**

Use the keywords: sharps disposal, needle exchange programs, biohazard waste disposal, safe needle disposal, metro[city].gov, recycling and disposal stations.

Seattle Children's offers free interpreter services for patients, family members and legal representatives who are deaf or hard of hearing or speak a language other than English. Seattle Children's will make this information available in alternate formats upon request. Call the Family Resource Center at 206-987-2201. This handout has been reviewed by clinical staff at Seattle Children's. However, your needs are unique. Before you act or rely upon this information, please talk with your healthcare provider.

© 2022 Seattle Children's, Seattle, Washington. All rights reserved.

11/22
PE612